# ተቃዋሚና ምሁር ነኝ ባይ ሁሉ እራሱን የሚወድ
# የአገር ኃላፊነትና ግደታን ተቀብሎ
# በተግባር የማይገልጽ ፈሪና ደካማ ነው

ከቀመሩ ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩን በቅጡ የሚያፈቅርና የሚወድ ኃይሉን አስተባብሮ የሚዋጋና የሚያሸንፍ ቆራጥ ፍቅር፣ ጥበብና ተስፋ ያለው ሕዝብ ነው ። እንኳን ወያኔ ባንዳ የባንዳ ልጅ ማፊያ አጋሚዶን ይቅርና ፋሽስት ወራሪዎችን፣ቅኝ ገዝዎችንና ተስፋፊዎችን አይቀጡ ቅጣት በመስጠት የቀጠና ድል የነሳ ነው ። ዛሬ በመታገሱ አሞቱ የፈሰሰና የተዳከመ እንዳይመስላችሁ ።በያለበት እንደ ነብር እያደባ ነው ።ተቃሚና ምሁር ነኝ ባይ ሁሉ እራስህን ወድደህ በመፍራት ከመሸማቀቅና ከመቅመድመድ ይህን የኢትዮጵያ ታሪክ በጥሩ ተገንዝበህና አውቀህ ለዚህም ኃላፊነትና ግደታ በቆራጥ ብሔራዊ የማንነት ስሜትና መንፈስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር መዋል ነው።

ዛሬ አገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ እየታመሰች የአገር ብሔራዊ ፍቅርና ስሜት ሲደበዝዝና ሲሸረሸር ለብሔራዊ አንድነት፣ ለታሪክ ክብርና ኩራት በድፍረትና በፅናት፣ ኃላፊነትና ግደታን የሚወስድ፣ ሕዝብን አሰባስቦ የሚመክርና የሚያደራጅ ተቃዋሚ ተማርን የሚሉ አገር ወዳድ ምሁራን መታጣታቸው ፣ ሰው የሚሆን ሰው መጥፋት የአገር መካንነት እጅግ የሚያሳዝን ጸጸትና ቁጭት እየሆነ ነው።

አገርን፣ ሕዝብንና ታሪክ እወዳለሁ፣ አከብራለሁ የሚል የተማረ ምሁር ፣ተቃዋሚ ድርጅት ነኝ የሚል ሁሉ የትውልድ ግደታና ኃላፊነት የማያውቅና የማይሰማው፣ የሚፈራና አንገቱን የደፋ፣በየጊዜ የሚንሸራተት፣ የሚሸሽና አገር ጥሎ የሚሰደድ ነው። የአገር ፍቅር የሕዝብ መውደድ የሚያጋየውና የሚሰማው በጋለና በማይሰክን የአገር ፍቅር ስሜት ታንጾ፣ በብስለት ወዳጅ ጠላትን በተገቢው ለይቶና አውቆ መሰለፍ። ለሕዝብ አለኝታ በድፍረት በመነሳሳት መሀል ዘልቆ በመግባት የሕዝብ አካል በመሆን ስልትና እቅድን ነድፎ ፣ አስተባብሮና አሰባስቦ፣አንቅቶና አስተምሮ፣አደራጅቶና አቅጣጫ በመስጠት እየመራ፣ በሕዝብ ታጅቦ ወደር የሌለው ኃይልን በመያዝ የወያኔ ጎጠኛ ከፋፋይ ጠላትን ከምድረ_ ኢትዮጵያ አርበድብዶና ድራሹን አጥፍቶ የሰላምና የደህንነት አገር ኢትዮጵያን ባደረገ ነበር።

እነዚህ እራስን የሚወዱ፣የራስ ጥቅምና ዝናን የሚፈልጉ፣ለሥልጣን የሚቋምጡ፣ትግል በጓደኝነት፣ በትውውቅ፣በመደጋገፍ ላይ ብቻ ሆኖ የሚታለመው እታይ እታይ አለሁ አለሁ በመሆኑ አገርና ወገን በመበደል ለበርካታ አገር ወዳድና የአንድነት ትግሉ ተቀርቋሪ አጋርን አስበርጋጊና እንድሸሹ በመደረጉ የአገርን ሕልው እየበደሉና እጐዱ ነው።ትግሉን እንዳሻቸው እየመሩ ሕዝብን ከማወክ ጋር ትልቅ የፖለቲካ ስህተትና ቅሌትን እየፈጸሙ ይገኛል። "ወዳጅ መስሎ ጠላት" ማለት ይህን መሰል አካሄድ ነው።

ተምሬ አለሁ ምሁር ነኝ፣የተቃዋሚ ድርጅት ነን ብቻ ሆኖ ፤ ፖለቲካዊ የተቃዋሚ ድርጅት ባህሪ የጐደለው፣ዓላማና ግቡን ያላመላከተ፣በቅጡ የማይመራና በየጊዜው የሚከፋፈል፣ መላቅጥ ያጣ በጠላት ላይ ያላነጣጠ ደካማና ተልካሻ መካን ስብስብ ሆኖ ይታያል።ማንም እራስን በመውደድና በማስቀደም የሚገሰግስ፣ የሚፈራና የሚያፈገፍግ የሚሸሽ፣የሕዝብ ፍቅር፣የአገር ስሜት የጐደለው ፣ኃላፊነትና ግደታን ተቀብሎ በተግባር የማይፈጽም ምሁር ነኝ ፣የተቃዋሚ ድርጅት ነኝ ማለት ከንቱ ፉከራና ሰሚ የሌለው

ማፏጨት ይሆናል ። አብዛኛው ወያኔን ገዢ ፓርቲ እያለ ተፎካካሪ ነኝ የሚል ሕገ መንግሥቱን የተቀበለ ከወያኔ የማይለይ በአምሳል የተፈጠረና ወያኔ ያጨቀየውን መንገድ ተከትሎ የሚዳክር ሲሆን አድርባዮ ደግሞ በወያኔ ጉያ ተደብቆ፣ እያደነቀና እያመሰገነ ለጥቅምና ለሆዱ ያደረ ተላላ ነው።

ከወያኔ ባንዳ ጋር በመተባበር ሲያዘርፉና ሲዘርፉ ፣ሲያስገድሉ የቀዮ ወንጀለኞች ሳይሳካላቸውና ሲገፈተሩ ተቃዋሚ ሆን የሚሉና ልዝብ፣ የወያኔን ጠላትነትና ጥፋት በውል ያልተረዱና ማወቅ የተሳናቸው ሲታሰሩ አጥፍቻለሁ፣ሕግን፣ እናንተንም አከብራለሁ፣እፈራለሁ ብሎ ይቅርታ የሚጠይቅና ሲቆጡት አገር ትቶ የሚፈረጥጥ ሁሉ ድርጅት፣ የሽግግር ምክር ቤት፣ የሽግግር መንግሥት (ሽንጎ) እያሉ ተላላ ተከታይ በመፍጠር የሚያላዝዙና ወያኔን የሚለማመጡ አብሮ ለመስራት እውቅና የሚሰጡ፣ ሳይታገሉና ሳያታግሉ ዋሽንግተን ዲሲ ተቀምጠው ሌላው ይታገል፣ በቆሰለበትና በሞተበት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለሥልጣን የሚቋምጡ ናቸው።

ከዚህ የተረፈው ደግሞ ድርጅት አልባ ሆኖ በየግሉ በትናጠል የሚጮህ ፣መላ ቅጡ የጠፋበት አንገቱን የደፋ ምሁር የተማረውን ሁሉ መሆን የሚፈልግ መማር፣ማወቅ ማንነትን ተረድቶ እራስን መሆን ዘንቶ ይገኛል።የተማረ ምሁርነት የመጡበትን ያለፈውን፣ ያሉበትን የዛሬውን አውቆና አገናዝቦ ያሉበትን ከመጭው ለይቶ በመረዳት የሚያልምና የሚያቅ፣ኃላፊነትና ግደታን በመገንዘበ የኅብረተሰብ አገልሎት ሰጭ፣አሳቢና ተቆርቋሪ ሆኖ መገኘት ነው።ነገር ግን በየደህረ ገጹ መቋጫ የሌለው ጹሁፍ መለጠፍ፣ ጨብጥ የሌለው ውሳኔ ማውጣት፣በሬዲዮ ቃለ መጠይቅ መስጠት፣ይህን አልኩ እያሉ መደንፋትና መጮህ ጠላትን የማያስደነግጥ የማይናከስ የውሻ ጩህት ነው።አገርን መውደድ ለሕዝብ መድረስና ለተጐዳው፣ ለተበደለው፣ ለደካማው፣ ለተራበው፣ለታረዘው፣ፍትህ ላጣው ኃላፊነትና ያገባኛል ብሎ ከጎኑ በመቆም ተደራጂቶ በማስተማር የሚመራና ለሙብት የሚያበቃ ሆኖ መገኘት ነው።ትውልድ ሁሉ በወቅቱ ኅብረተሰብ አንገቱን ቀና አድርጐ እንዲሄድ፣አገር ዘለግ ብላና ከሌሎች ቀድማና ጐልታ እንድትታይ የሚጥርና የሚያስቀድም ስራን መስራት ነው።

ሁላችሁም እንደምታውቁት የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአቅጣጫው እየተሰቃየና አገሪቱ በየቦታው እተቦረቦረች ይገኛሉ።እነዚህ ተቃዋሚ ስብስብ ድርጅትና ምሁር ነን ባዮች ፈሪዎችና ደካሞች ሕዝብን ለመርዳት ዛሬም_ነገም_ ወደፊትም ፈቃደኞች አይደሉም፣ አይጠቅሙም።ተስፋ ማድረግና መርዳት ያለብን የፖለቲካው ባለቤት የኢትዮጵያ ሕዝብን ነው።ስለዚህ ሁላችንም በየአቅጣጫው ሕዝቡን እንቀስቅስ እንርዳ።ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የሚወዳትና የሚያግዛት ቅዱስ አገር ናት፣ ዳግም ታፍራና ተከብራ ትኖራለች።

## መሪ ከሕዝብ መሀል ይወለዳል!

## ምንጊዜም ኢትዮጵያ !

04/19/2013